AMHARIC

# ጎረቤቶች ጎረቤቶችን ሲረዱ በረዶን በአካፋ የመዛቅ ፕሮግራም

በዚህ ክረምት በፈቃደኝነት እና በችግር ላይ ያሉ ጎረቤቶችዎን መርዳት ይፈልጋሉ? የሲያትል ከተማ የማህበረሰቡን የበረዶ በአካፋ የመዛቅ ጥረቶችን ለመደገፍ የሙከራ ፕሮግራም ጀምራለች። ግቡ አረጋውያን እና የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ሰዎች በቤታቸው አቅራቢያ ያሉትን የእግረኛ መንገዶችን እና የእግረኛ መረማመጃዎችን በማጽዳት ከበሩ እንዲወጡ መርዳት ነው።

## እንዴት እንደሚሰራ እነሆ:

- **ፍላጎት ያላቸው በጎ ፈቃደኞች እና በረዶን በአካፋ የመዛቅ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ አባላት፡-** ለብሎክዎ እቅድ ለማውጣት የአካባቢዎትን ብሎክ ቃኚ ካፒቴን ያነጋግሩ።
- **የእርሰዎ ብሎክ ቃኚ ካፒቴን ማን እንደሆነ አታውቁም?** ወደ የሲያትል ፖሊስ ዲፓርትመንት ድህረ ገጽ የብሎክ ቃኚ ገጽ ይሂዱ እና ለአካባቢዎ የወንጀል መከላከል አስተባባሪ (ሲፒሲ) ያግኙ።
- **ለመንገድዎ ብሎክ የሚከታተል ካፒቴን የለዎትም?** በአቅራቢያዎ ስለ ብሎክ ቃኚ (Block Watch) ቡድኖች ወይም እርሰዎ ሊገናኙዋቸው ስለሚችሉ ሌሎች የበጎ ፈቃደኞች ድርጅቶች ለመጠየቅ የአካባቢዎ CPCን ያነጋግሩ።

## የበለጠ ለማወቅ:

- የሲያትል የብሎክ ቃኚ ፕሮግራም፡- seattle.gov/police/crime-prevention/block-watch
- የSDOT የክረምት የአየር ሁኔታ ድር ጣቢያ፡- seattle.gov/transportation/winter-weather

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወደ የሲያትል የትራንስፖርት መምሪያ (SDOT) የደንበኛ እንክብካቤ ቡድን በ (206) 684-ROAD ወይም 684-ROAD@seattle.gov ላይ ማግኘት ይችላሉ።

የሲያትል ከተማ በጎ ፈቃደኞችን በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ ሊረዳ ይችላል:

- አካፋዎች
- የበረዶ መቅለጥ
- የአካፋ አጠቃቀም ምክሮች

* አቅርቦቶች እስከምያልቁ ድረስ




City of Seattle